አማርኛ

**AMHARIC**

የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶልን

# ለመጎብኘት ያቅዱ

U.S. CAPITOL
የጉብኝት ማዕከል

www.visitthecapitol.gov

## የጉልላት እድሳት ፕሮጀክት

የዩኤስ ካፒቶል የጉልላት እድሳት ፕሮጀክት የጉልላቱን ዉጫዊ እና ውስጣዊ አካሎች ለማደስ ታስቦ እየተከናወነ ይገኛል። ለመጨረሻ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እድሳት የተደረገለት ከ1959 - 1960 በነበረዉ ወቅት ሲሆን በብረት ላሜራ የተሰራዉ ጉልላት በአየር ጸባይ ተጽእኖ እና በእድሜ መርዘም ምክንያት የደረሰበት ችግር ዝገት እና መሰነጣጠቅን ይጨምራል።

በፕሮጀክቱ የሚከናወኑት ተግባራት በላሜራ የተሰሩትን ታሪካዊ የጉልላቱን አካሎች የማደስ ስራ፣ ዉጫዊዉ አካሉ የአየር ንብረት እንዲቋቋም ማድረግ፣ የተሰበሩ መስኮቶችን መቀየር እና ለጤና ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉ ቁሶችን ማስወገድን ያጠቃልላል። በዚህ ፕሮጀክት የትግበራ ወቅት የህንጻውን ውጫዊ አካል አቅፎ የሚይዝ ወጋግራ የሚሰራለት ከመሆኑ በተጨማሪ በካፒቶሉ ህንጻ ሁለተኛው ደርብ ላይ የሚገኘው ሮተንዳ 96 ጫማ የክበብ አጋማሽ ርዝመትና 180 ጫማ ከፍታ ያለው ትልቅ ክብ ክፍል ውስጥ ለደህንነት ሲባል የተወጠረ መረብ ይዘረጋል።

ፕሮጀክቱ የ2017 የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝደንት የሹመት በዓል ከመድረሱ በፊት እንዲጠናቀቅ በእቅድ ተይዟል።



**የጉልላት እድሳት ፕሮጀክቱ የተወሰነ ደረጃ ላይ ሲደርስ ወጋግራዎችና የስእል ስራዎችን ከጉዳት መጠበቂያዎች ሊደረጉ ይችላሉ።**

## የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል እና ኮንግረስ

**የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል** ሐዉልት፣ ስራ የሚሰራበት የቢሮ ህንጻ ከመሆኑ በተጨማሪ በዓለም ላይ በጣም ከሚታወቁት **የዉክልና ዴሞክራሲ** መገለጫ ምልክቶች መሀከል አንዱ ነዉ።

በህግ አወጣጥ ዙሪያ በሚደረግ የክርክርና የማቻቻል ሂደት **የዩኤስ ኮንግረስ ህጎችን ያወጣል** እነዚህም ህጎች በዜጎች የእለት ተእለት ኑሮ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። ኮንግረሱ የህግ አወጣጥ ሂደቱ በቂ መረጃ እንዲኖረው ጉዳዩን የሚያዳምጥ ጉባዔ ያካሂዳል፣ የስራ አስፈጻሚዉን ቅርንጫፍ በበላይነት ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ምርመራ ያካሂዳል፣ በፌዴራል መንግስቱ ውስጥ የተካተቱትን ግዛቶች ጥቅም በማስጠበቅና የህዝቡ ድምጽ በመሆን ያገለግላል።



የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል

**ኮንግረስ የፌዴራል መንግስቱ ህግ አዉጪ ቅርንጫፍ ነው** ይህም የአሜሪካንን ህዝብ በመወከል ሀገሪቱ የምትተዳደርበትን ህግ ያወጣል። በመሆኑም በፕሬዚደንቱ ከሚመራዉ የስራ አስፈጻሚ አካልና የዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍተኛ አካሉ ከሆነው ከህግ አስፈጻሚው አካል ጋር ስልጣን ይጋራል። ከሶስቱ የመንግስት አካሎች ውስጥ በቀጥታ **በህዝብ** የሚመረጥ ኮንግረስ ብቻ ነዉ።



**የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት መሰብሰቢያ አዳራሽ**



**የሴኔት መሰብሰቢያ አዳራሽ**

**የዩኤስ ዜጋ ያልሆኑ ጎብኚዎች የህዝብ ተወካዩች ወይም የሴኔት መሰብሰቢያ አዳራሽ መጎብኘት የሚፈቀድላቸዉ ሲሆን አስቀድሞ በነጻ የሚታደለዉን የይለፍ ፈቃድ በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል የላይኛዉ ደርብ ላይ ከሚገኘው የቀጠሮ ዴስክ ማግኘት ይቻላል።**

**አንቀጽ 1** — በጣም ረጅሙ **የዩኤስ ህገ መንግስት** አንቀጽ — የኮንግረስን ስልጣን ይዘረዝራል። ኮንግረስ ህግ የማውጣት፣ ጦርነት የማወጅ፣ የህዝብ ገንዘብ የማዘጋጀት እና የማቅረብ እንዲሁም ገንዘቡ በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን የመቆጣጠር፣ የፌደራል ባለስልጣናትን የመክሰስና ጉዳያቸውን አይቶ ፍርድ የመስጠት፣ በፕሬዝደንቱ የሚቀርቡ ተሿሚዎችን ሹመት የማጽደቅ እና የስራ አስፈጻሚዉ አካል የተደራደራቸውን ስምምነቶች የማጽደቅ ስልጣን አለው።

ኮንግረስ በሁለት ተቋማት የተከፈለ ነዉ፦ **የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ሴኔት።** ሁለቱ ምክር ቤቶች ያላቸዉ ስልጣን እኩል ቢሆንም በፌዴራል መንግስቱ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ግን የተለያየ ነዉ።

የዩኤስ ካፒቶል ህንጻ **የኒዎክላሲካል ኪነ ህንጻ** ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል። የህንጻዉ ዲዛይን ከጥንታዊያን የግሪክ እና የሮም ኪነ ህንጻዎች የተገኘ ሲሆን የሪፐብሊኩ መስራች የሆኑት መሪዎች አዲሱን ሪፐብሊክ ለመመስረት በወቅቱ ያነሳሳቸው የነበረዉን እሳቤዎች የሚያንጸባርቅ ነው። በህንጻዉ ውስጥ ግርማ ሞገስ ያላቸው ስእሎች፣ ሀውልቶች፣ እንዲሁም **በአሜሪካ ታሪክ** ውስጥ ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸዉን ምእራፎች የሚዘክሩ የስነ ጥበብ ስራዎችን ያያሉ።

## ካፒቶል እንደ የሀገሪቷ የትእይንት መድረክ

ካፒቶል ከሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች አንዱ በሀገሪቷ ውስጥ የሚከናወኑ **ዋና ዋና የህዝብ በአላትን** ማስተናገድ ሲሆን በሀዘን ድባብ ውስጥ ከሚከበሩ ዝክረ በአላት እስከ ደስ እስከሚለው ጁላይ ፎር የነጻነት በዓል የሙዚቃ ዝግጅት ያለውን ሁሉንም ያስተናግዳል። በሮተንዳ ውስጥ ሀዘንተኞች በጸጥታ ሆነው በሞት የተለዩ ፕሬዚደንቶችንና ታላላቅ ሰዎችን አስከሬን በክብር ተቀምጦ ባለበት በሀዘን ተሰናብተዋል። **የፕሬዚደንቶች በዓለ ሹመት** በካፒቶሉ ምእራባዊ በረንዳ የሚከናወን ሲሆን **የኮንግረስ የወርቅ ሜዳልያዎች** ታላቅ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ግለሰቦች የሚበረከተዉም በዚሁ ስፍራ ነዉ። በተጨማሪ በጉልላቱ ጥላ ስር ያለው ቦታ በርካታ የህዝብ በአላት የሚከበሩባቸው መድረኮች ናቸው። ብቻቸውን ሆነዉ ንግግር ከሚያደርጉ ግለሰቦች እስከ ህዝባዊ ሰልፎች ድረስ ሰዎች ለመስማት ሲሉ እዚህ ስፍራ ይመጣሉ።



የካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ወደ ዩኤስ ካፒቶል የሚያስገባ ዋናዉ መግቢያ ነዉ።




ከእንግሊዝኛ ውጪ በሆኑ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የፒዲኤፍ ፋይሎች ከድረ ገጽ ላይ [www.visitthecapitol.gov/brochures](http://www.visitthecapitol.gov/brochures) ማዉረድ ይችሉ ይሆናል።



ከእንግሊዝኛ ሌላ በሆኑ ቋንቋዎች የተዘጋጁ በራሪ ጽሁፎች በጎብኚዎች ማእከል ይገኛሉ።

# የካፒቶል ጉብኝት

**ወረፋ መያዝ** - የካፒቶል ጉብኝ ያለ ክፍያ በነጻ ይከናወናል።

ጉብኝት ለማድረግ ወረፋ መያዝ ከፈለጉ በድረ ገጽ [Advance Reservation System](#) ወይም በጎብኚዎች አገልግሎት ቢሮ ስልክ (202) 226-8000 መደወል ይችላሉ።

**የካፒቶል ጉብኝት የይለፍ ፈቃድ** - **በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ሲደርሱ ለጉብኝቱ አስቀድመዉ ወረፋ ይዘው** የወረፋ ማረጋገጫ ወይም የወረፋ ማረጋገጫ ቁጥር ይዘው ከሆነ እባክዎ ወደ ታችኛዉ የህንጻዉ ደርብ በመሄድ በቀኝ በኩል በሚገኘዉ የመረጃ ዴስክ የሚታደለዉን **የካፒቶል ጉብኝት የይለፍ ፈቃድ ይዉሰዱ።** ይህ ለደህንነት ሲባል ጎብኚዎች በልብሳቸዉ ላይ የሚለጥፉት ስቲከር እርስዎ ከተወሰነ የጉብኝት ቡድን ጋር መሆንዎን የሚያረጋግጥ ነው።

አስቀድመዉ የካፒቶል ጉብኝት ቀጠሮ ሳይዙ ካፒቶል ከመጡ በጎብኚዎች ማእከል የታችኛዉ ደርብ ባለዉ በመረጃ ዴስኩ በግራ በኩል ወደ ሚገኘዉ "Public Walk-up" በመሄድ ሰልፍ ይያዙ። ለእለቱ የሚያገለግሉ የጉብኝት የይለፍ ፈቃድ ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል። የጎብኚዎች ቁጥር በሚጨምርባቸዉ ወቅቶች ማለትም በጸደይ እና በበጋ ወቅቶች ለእለቱ የሚታደሉ የጉብኝት የይለፍ ፈቃዶችን ማግኘት ቀላል ላይሆን እና ረዥም ሰልፍ መጠበቅ ግድ ሊሆን ይችላል።

እባክዎ ያስታውሱ፡ *በዩኤስ ካፒቶል የሚደረግ ጉብኝት እቅድ ባልተያዘላቸው በተለያዩ ምክኒያቶች ሊቋረጥ ይችላል። እንዲህ አይነት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ማስታወቂያዎች በድረ ገጽ www.visitthecapitol.gov እና በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ ይለቀቃሉ።*

**ከካፒቶል ጉብኝት ምን ይጠበቃል** - በአጠቃላይ በዩኤስ ካፒቶል የሚደረጉ ጉብኝቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሙያዉ በሰለጠኑ አስጎኚዎች የሚከናወኑ ናቸው። እነዚህ በአስጎብኚዎች እገዛ የሚከናወኑት ጉብኝቶች የሚጀምሩት "Out of Many, One," የሚል ርእስ ባለው አገሪቱ በዓለም የመጀመሪያ የሆነውን እውነተኛ የውክልና ዲሞክራሲ ለመመስረት ያለፈችበትን ትግልና የዩኤስ ኮንግረስ የሚገኝበትን ድንቅ የሆነ ህንጻ በሚያስተዋውቅ 13 ደቂቃ በሚፈጅ ማስተዋወቂያ ፊልም ነው። መደበኛ የካፒቶል ጉብኝት ጎብኝዎችን በክሪፕት፣ በሮተንዳውና በብሄራዊ የሀውልቶች አዳራሽ በኩል እንዲያልፉ ያደርጋል። *ለደህንነት ሲባል ጎብኚዎች በሙሉ በማንኛውም ግዜ እባካችሁ ከአስጎብኛችሁ (ቀይ ጃኬት የሚለብሱ) ጋር አብራችሁ እንድትቆዩ እንመክራለን።*

**የዚህን የማስተዋወቂያ ፊልም በአለማቀፍ ቋንቋዎች ለመስማት የማዳመጫ መሳሪያዎች** ያስፈልገኛል ብለው በካፒቶል የጎብኝዎች ማዕከል ካለው የመረጃ ዴስክ ከጠየቁ ሊያገኙ ይችላሉ። በማዳመጫ መሳሪያ ሊሰሙ የሚችሉ በአሁኑ ወቅት ተዘጋጅተው ያሉ ቋንቋዎች፡- ስፓንሽኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ጃፓንኛና የማንዳሪን ቋንቋ ናቸው። *(እነዚህን የማዳመጫ መሳሪያዎች በነጻ መጠቀም የሚቻል ሲሆን ጎብኚዎች ማዳመጫዎቹን ከመረጃ ዴስክ ለመዋስ አንድ ፓስፖርት ያልሆነ ፎቶግራፍ ያለበት ማዳመጫው ሲመለስ የሚመለስ መታወቂያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።)*

**የካፒቶል ጉብኝትን ከሚካሄደው ጉብኝት ጋር ለመከታተል የሚረዱ በራሪ ወረቀቶች** የጉብኝቱን ዋና ትኩረት አጉልተው የሚያሳዩ ሲሆን ወረቀቶቹን በጎብኚዎች ማእከሉ የታችኛዉ ደርብ ካለዉ የመረጃ ዴስክና የካፒቶል ጉብኝት ከሚጀምርበት ቦታ ከአስጎብኚዎች ማግኘት ይችላሉ። በአሁኑ ግዜ ያሉ ቋንቋዎች፡- አማርኛ፣ አረብኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ሂንዲኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ጃፓንኛ፣ ኮርያንኛ፣ ፖርቱጋልኛ፣ ሩሲያኛ፣ ስፓንሽኛና ቬትናምኛ ናቸው። *(ሌሎች ጎብኝዎች መረጃዎቹን ማግኘት እንዲችሉ እባክዎ ጉብኝትዎን ከጨረሱ በኋላ በራሪ ወረቀቶቹን ለጉብኝት መሪዎ ይመልሱ።)*



ኢማንስፔሽን አዳራሽ የጎብኚዎች ማእከሉ ዋነኛዉ ክፍል ሲሆን ኢማንስፔሽን አዳራሽ ውስጥ ያለዉ ከአሸዋማ ድንጋይ የተሰራው የባሪያ ጉልበት መዘከሪያ ምልክት በወቅቱ በባርነት የነበሩት ሰዎች ካፒቶልን በመገንባት ስራ ላይ የነበራቸዉን አስተዋጽዎ የሚዘክር ነዉ።




የጎብኚዎች የይለፍ ፍቃድ (ስቲከሮች) በካፒቶል ውስጥ በነጻ የሚሰጡ ሲሆን በካፒቶል ውስጥ ጉብኝት ለማድረግ አስፈላጊ ናቸው። ስቲከሮቹ በኢማንስፔሽን አዳራሽ የመረጃ ዴስክ ይገኛሉ።

የካፒቶል ጉብኝት የሚጀምረው 13 ደቂቃ ርዝመት ባለዉ የማስተዋወቂያ ፊልም ነው። ከእንግሊዝኛ ሌላ ለሆኑ ቋንቋዎች የፊልም ማዳመጫ መሳሪያዎችን ከመረጃ ዴስክ በመጠየቅ ሊያገኙ ይችላሉ። ሌሎች ጎብኚዎችን ለማክበር ሲባል ፊልሙ ከመጀመሩ በፊት የእጅ ስልክዎን ድምጽ ያጥፉት። በትያትር ቤቱ ውስጥ ፎቶግራፍ ማንሳት አይፈቀድም።



## የምክር ቤት እና የሴኔት ጋለሪዎች

**የምክር ቤት እና የሴኔት ጋለሪዎች** - የሴኔት እና የምክር ቤት ጋለሪዎች ከሁለት አንዱ የህግ አውጭ አካል በስራ ላይ በሚሆንበት ወቅት ለጎብኚዎች ክፍት ይሆናሉ ሆኖም ግን የጋለሪዎቹ ጉብኝት ከዩኤስ ካፒቶል ጉብኝት ጋር አብረው እንዲሆኑ አልተደረገም። የትኛውንም ጋለሪ ለመጎብኘት የይለፍ ፈቃድ ያስፈልጋል። ጎብኚ የሆኑ የዩኤስ ዜጎች ጋላሪዎቹን ለመጎብኘት ሲፈልጉ ከመጡበት ግዛት ሴኔተሮች ቢሮ ወይም ከእንደራሴዎቻቸዉ ጽ/ቤቶች የይለፍ ፈቃዶቹን ማግኘት ይችላሉ። ዓለም አቀፍ ጎብኚዎች በካፒቶል የጎብኝዎች ማዕከል በላይኛው ደርብ ላይ ከሚገኙት ከምክር ቤቱና ከሴኔት የቀጠሮ ዴስኮች ሊጠይቁ ይችላሉ።




የሴኔት ጋለሪዉ ክፍት መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ሲፈልጉ በ(202) 224-0057 ደዉለዉ ይጠይቁ።

ወደ ምክር ቤት እና ወደ ሴኔት ጋለሪዎች የሚያስገባው መግቢያ ያለው በጎብኚዎች ማእከሉ የላይኛዉ ደርብ ነው (መግቢያዎቹ ያሉት በተሽከርካሪ ደረጃዎቹ በቀኝና በግራ በኩል ነው)።

## የትእይንት አዳራሽ ሙዚየም

**የትእይንት አዳራሽ ሙዚየም** - የትእይንት አዳራሹ የዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስንና የዩኤስ ካፒቶል ታሪኮችን ለመዘከር የተቋቋመ በዓለም ብቸኛዉ ኤግዚቢሽን ነዉ። ኦሪጅናል ሰነዶችና እቃዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ሊነኩ የሚችሉ ናሙናዎች፣ የኮምፒውተር መልስ ሰጭዎችና ለጎብኝዎች ኮንግረስ እንዴት እንደሚሰራ፣ የካፒቶልና የኮንግረስ ታሪክ እንዲሁም የህዝብ ተወካዮችና ሴነተሮችን መረጃ አስመልክቶ ጠለቅ ያለ መረጃ የሚያቀርቡ ሁለት ትናንሽ የትእይንት ክፍሎች የተካተቱት በዚሁ


አማርኛ > AMHARIC

U.S. CAPITOL

የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል ጉብኝት

የጉብኝት ሂደቱን መከታተያ ከእንግሊዘኛ ሌላ በ13 ቋንቋዎች የተዘጋጁ በራሪ ጽሁፎችን ከአስጎብኝዎ ወይም በመረጃ መስጫ ዴስኮች ተዘጋጅተው አሉ። እባክዎ የጉብኝት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት እነዚህን ጽሁፎች ይጠይቁ።



ወደ ኤግዚቢሽኑ አደራሽ የሚያስገባው መግቢያ ያለው በነጭ ጄሶ የተሰራ የነጻነት ሀውልት ናሙና ካለበት በስተጀርባ ነው። ከዚህ ናሙና በመነሳት በነሀስ የተሰራዉ የነጻነት ሀዉልት በካፒቶል ጉልላት ላይ ተቀምጦ ይገኛል።

በኤግዚቢሽን አዳራሽ ውስጥ ነው። የኤግዝቢሽን አዳራሹ መግቢያ በጎብኚዎች ማእከሉ የታችኛዉ ደርብ በነጭ ጄሶ ከተሰራው የነጻነት ሀውልት ናሙና በስተጀርባ ነው።

**ልዩ ተግባራት** - ልዩ ጉብኝቶች፣ ንግግሮችና የቤተሰብ ፕሮግራሞች ብዙውን ግዜ በጎብኚዎች ማእከሉ ይቀርባሉ። እነዚህ ልዩ ዝግጅቶች ስለመኖራቸው "ይህ ሳምንት በካፒቶል የጎብኝዎች ማእከል" በሚል የመልክት ማሰራጫ በእንግሊዘኛ በድረ ገጽ www.visitthecapitol.gov ላይ ወይም በሶሻል ሚዲያ ይለቀቃሉ።

## የጎብኚ መረጃ

**የስራ ሰዓቶች** - የካፒቶል ጉብኝት ማዕከል ለጎብኝዎች ወደካፒቶሉ እንደ መግቢያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ክፍት የሚሆነውም ከጠዋቱ 8:30 እስከ ከሰዓት 4:30 ድረስ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከዩኤስ ብሄራዊ ክብረ በዓል ቀናት በስተቀር ባሉት ቀናት ነው። በየእለቱ የመጨረሻዉ ካፒቶል ጉብኝት የሚጀመረው ከሰዓት በኋላ በ3:20 ላይ ነዉ።

**የጎብኚዎች መግቢያ** - ለጎብኚዎች የሚያገለግለዉ መግቢያ ምድር ቤት ውስጥ ሆኖ በካፒቶሉ ምስራቅ ጎን በኩል ከምስራቃዊው ፐላዛ ስር በአንደኛው መንገድና በኢስት ካፒቶል መንገድ መጋጠሚያ ላይ በሚገኘው በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ውስጥ ነው ይህም ማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ እና በላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ የቶማስ ጀፈርሰን ህንጻ ፊት ለፊት ካለው መንገድ ማዶ ላይ ነው። አስፈላጊ በሆኑት የደህንነትና የፍተሻ ሂደቶች እንዲሁም ብዙ ጎብኝዎች በሚመጡባቸው ወቅቶች ረጅም ሰልፍ ሊኖር ስለሚችል የጉብኝት ሰዓትዎ ከመድረሱ ከ45 ደቂቃ በፊት በመድረስና በካፒቶሉ ምድር ይዘው መገኘት የማይገባዎትን ከመያዝ እንዲቆጠቡ ልናሳስብዎ እንወዳለን።

**ደህንነት** - የካፒቶል ጉብኝት ፖሊሲዎች የተዘጋጁት የጎብኚዎችን እና የሰራተኞችን ደህንነት ታሳቢ በማድረግና ስብሰቦችን፣ መገልገያዎችንና ታሪካዊውን ህንጻና በዙሪያዉ ያለዉን ስፍራ ደህንነቱ ተጠብቆ ለቀጣይ ትዉልዶች እንዲተላለፍ ለማድረግ ነው።

### የደህንነት ፍተሻ

በካፒቶል ጉብኝት የሚያደርጉ ጎብኝዎች በሙሉ በደህንነት መፈተሻ ውስጥ ማለፍ አለባቸው።

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እቃዎች በካፒቶልም ሆነ በጎብኚዎች ማእከል ይዞ መገኘት ፈጽሞ የተከለከለ ነው:-



- ፈሳሽ፣ ውኃንም ጨምሮ
- ምንም ዓይነት ምግብ፣ ፍራፍሬዎችን እና ያልተከፈቱ የታሸጉ ምግቦችን ጨምሮ
- 18 ኢንች ስፋት በ14 ኢንች ርዝመት እንዲሁም 8.5 ኢንች ጥልቀት በላይ የሆነ ማንኛዉም ቦርሳ ይዞ መግባት አይፈቀድም
- ፍሊቶች
- በውስጡ ንፋስ የሌለው ፍሊት (በሀኪም የታዘዙ የህክምና አገልግሎት እቃዎች ይፈቀዳሉ)
- ሽጉጦች፣ የመጫወቻ ሽጉጦች ፣ በኤሌክትሪክ የሚያነዝሩ ሽጉጦች፣ ጥይቶችና ርችቶች
- በመጠኑ ትልቅም ሆነ ትንሽ የሆኑ ቢላዎች
- አይንን የሚለበልብ የሚረጭ ፍሊት
- የማርሻል አርት መሳሪያዎች ወይም እቃዎች
- ምላጮች እና የካርቶን መቁረጫ ስለቶች



ካፒቶሉ ባረፈበት ምድር ሁሉ በቀላሉ መንቀሳቀስ ለማይችሉ ወይም በእጅ በሚገፉ ተሽከርካሪ ወንበሮች ላይ ሆነው ለሚዘዋወሩ ሰዎች የሚሆን የማመላለሻ አገልግሎት አለ።




ሬስቶራንቱ በጎብኚዎች ማእከሉ የታችኛዉ ደርብ ላይ ይገኛል።




በጎብኚዎች ማእከሉ የላይኛው ደርብ ላይ ሁለት የስጦታ እቃ መሸጫ መደብሮች ይገኛሉ።

ወደ ካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ከመግባትዎ አስቀድሞ ሁሉም ጎብኚዎች በማግኒቶሜትር የሚፈተሹ ሲሆን በህንጻዉ ውስጥ ይዘው ሊገቡ የሚፈቀድልዎት እቃዎች በሙሉ በኤክስሬይ መሳሪያ ይታያሉ። እባክዎ በገጽ 5 ላይ በሳጥን ያለውን ወይም የተከለከሉ እቃዎች የሚለውን ይመልከቱ።

የዩኤስ ካፒቶል ፖሊስ እንደየአስፈላጊነቱ ከመመሪያው ውጭ የተከለከሉ እቃዎች ለልጆች እንክብካቤ፣ ለህክምና ወይም ልዩ ለሆኑ አገልግሎቶች አስፈላጊ ሆነው  ሲገኙ ተይዘው እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል። ቦርሳዎች በካፒቶል ፖሊስ ፍተሻ ሊደረግባቸዉ ይችላል።

**መግባት ስለመቻል** - ጎብኚዎች ማንኛውንም ቀይ ሰደርያ ወይም ጃኬት የለበሰ የካፒቶል የጉብኝት ማዕከል ሰራተኛን ወይም ልክ በዋናው መግቢያ እንደገቡ ካፖርት ከማቆያው ጣቢያ በጎማ የሚሽከረከር ወንበር ሊጠይቁ ይችላሉ።  በጎማ የሚሽከረከረውን ወንበር ለማግኘት ፓስፖርት ያልሆነ ፎቶ ግራፍ የተለጠፈበት መታወቂያ ያስፈልጋል።  ካፖርት የመቀበያው ጣቢያ በየዕለቱ ከሰዓት ልክ በ4:15 ላይ ይዘጋል።

አስቀድመው ላሳወቁ ጎብኚዎች በጉብኝቱ ወቅት የምልክት ቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።

በድምጽ የፊልሞችንና ኤግዚቢሽኖችን የእንግሊዘኛ ገለጻ የማዳመጫ መሳሪያዎች በመረጃ ዴስኮች ይገኛሉ።  ሁሉም ፊልሞች በግልጽ የሚታይ የእንግሊዘኛ የገለጻ ጽሁፍ አላቸው።  የበራሪ ወረቀት ኮፒዎች በብሬል፣ በትልቅ ህትመትና በhtml ፎርሞች ተዘጋጅተው በኢማንሲፔሽን አዳራሽ ውስጥ በሚገኙ የመረጃ ዴስኮች ይገኛሉ።

በካፒቶል ውስጥ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው ወይም በእጅ በሚገፉ ተሽከርካሪ ወንበር ለሚንቀሳቀሱ የማመላለሻ አገልግሎት አለ። እነዚህ የማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሚመላለሱት ከካፒቶል አደባባይ ከደቡባዊ ምእራብ ጥግ በኢንዲፔንዳንስ ጎዳና እና አንደኛ መንገድ SW እስከ ካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የካፒቶሉ ምስራቃዊ ፕላዛ መህል ድረስ ነው።

በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል የሚገኙት ሁሉም መጸዳጃ ቤቶች ለጎብኚዎች ተደራሽ  ናቸው።

**የኮንግረስ ተደራሽነት ግልጋሎት ጽ/ቤትን ለማግኘት በ(202) 224-4048** (በድምጽ) ወይም (202) 224-4049 (TTY) ይደውሉ።

**ፎቶግራፍ** - በጎብኚዎች ማእከሉ ፎቶግራፍ ማንሳት ይፈቀዳል። ሆኖም ግን በኤግዚቢሽን ማእከሉ ሙዚየም አዳራሽ ውስጥ ፎቶግራፍ ማንሳት ፈጽሞ የማይፈቀድ ሲሆን ይህም የሆነው በማእከሉ የሚገኙ ኦሪጅናል ታሪካዊ ሰነዶችን ከጉዳት ለመከላከል በማሰብ ነዉ። በካፒቶል ጉብኝት መጀመሪያ ላይ የሚታየዉ የጎብኚዎች ማስተዋወቂያ ፊልም በሚታይበት ወቅት ፎቶግራፍ ማንሳት አይፈቀድም። ፎቶግራፍ ማንሳት የሚፈቀደዉ በክሪፕት፣ በሮተንዳ እና በብሄራዊ የሀውልቶች አዳራሽ ጉብኝት ወቅት ብቻ ነዉ።

## የካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል

**ሬስቶራንት** -  ሬስቶራንቱ በታችኛዉ የህንጻዉ ደርብ የሚገኝ ሲሆን የተለያዩ ኮንትኔንታል ቁርሶችን ከጠዋት 8፡30 እስከ 11፡00 እንዲሁም ምሳ 11፡00 እስከ ከሰዓት 4፡00 ድረስ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ባሉት ቀናት ያቀርባል። እዛው የተሰሩ ሾርባዎች፣ ሰላጣ፣ ልዩ ምግቦች፣ ፒዛዎች፣ ሳንድዊቾች፣ ጣፋጭ ምግቦችና ልዩ ልዩ ለስላሳ መጠጦች የሚቀርቡበት ሲሆን ይህም አሜሪካ የታደለቻቸውን የተለያዩ በረከቶችን እንዲያንጸባርቁ ሆነው በሬስቶራንቱ ለሽያጭ ቀርበዋል።



የካፒቶል የምእራብ አካል ፊቱ ወደ ናሽናል ሞል በኩል ነው።



“My Capitol” የካፒቶልንና የኮንግረስን ያለፈ ታሪክ፣ እንቅስቃሴዎችንና ውይይት የሚያጭሩ ጥያቄዎችን አጠቃሎ የያዘ ትእይንት አዳራሹ ውስጥ ራስዎን በራስዎ እየመሩ እንዲጎበኙ የሚያደርግዎ መጽሀፍ ነው። ወላጆችና አስተማሪዎች “My Capitol” መጽሀፍቶችን በጎብኝዎች ማዕከል በላይኛው ደርብ በስተሰሜን በኩል ካለው የካፖርት ማስቀመጫ ሊወስዱ ይችላሉ። በድረ ገጽ PDF የተዘጋጁ ጽሁፎች አሉ። በApp Store እና በGoogle Play የ“My Capitol” app ይገኛል። የዚህ አነስተኛ መጽሀፍ የተለያዩ እትሞች በሙሉ የተዘጋጁት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው።

**የስጦታ እቃ መሸጫ መደብሮች** - የስጦታ እቃ መሸጫ መደብሮቹ በላይኛዉ ደርብ ሚገኙ ሲሆን ከጠዋቱ 9:00 እስከ ከሰዓት 4:30 ድረስ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ክፍት ናቸዉ። የስጦታ መደብሮቹ የሚያቀርቧቸው በካፒቶል ባሉ ብዛት ባላቸው ስእሎችና አርክቴክቸር ላይ መሰረት ያደረጉ፣ ደስ እሚሉና ትምህርታዊ የሆኑ ስጦታዎች፣ ምጽሀፍቶች፣ ጌጣ ጌጦችና ሌላ ቦታ የሚይገኙ ስሜትን የሚቀሰቅሱ በልዩ ንድፍ የተሰሩ ውጤቶች ናቸዉ።

## ለተጨማሪ መረጃ

*(የሚቀጥሉት መረጃዎች በእንግሊዝኛ የቀረቡ ናቸዉ)*

### APPS

apps.visitthecapitol.gov

የካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል Rotunda app ለጎብኚዎች የሚከተሉትን ግልጋሎቶች ይሰጣል፦

- 360 ዲግሪ ዙሪያ ገብ ምስል በሚያሳይ ኢሜጂንግ አማካይነት ሮተንዳዉን በአካል እንደሚያዩት አድርጎ ማሳየት
- በሮተንዳው ውስጥ ስለሚገኙ ስለያንዳንዳቸው ሀውልቶችና ስእሎች ማስተማር
- በሮተንዳው ጣሪያ ላይ ተስሎ የሚገኘውን የፍሪስኮ ስእል በቅርብ ማየትና መገንዘብ መቻል
- በሮተንዳው ውስጥ ስለሚካሄዱት ዝግጅቶች በደንብ እንዲያውቁ ... እና ብዙ ሌሎችንም ይጨምራል።




**ሌሎች የካፒቶል ጎብኚዎች ማእከል** apps የሚያካትታቸው የጎብኚዎች መመሪያ፣ በካፒቶል ውስጥ ያሉ የግዛት ሐዉልቶች መጠቀሚያ እንዲሁም ለወጣቶች የተዘጋጀዉ “My Capitol” ናቸው። ሁሉም በApp Store እና Google Play ይገኛሉ።

### ማህበራዊ ሚዲያ

Twitter@visitthecapitol

የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል ዩቱብ ቻናል

የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ፌስቡክ



በኢማንስፔሽን አዳራሽና በካፒቶል ህንጻ ውስጥ የሚገኙት ሀዉልቶች የአሜሪካን ብዝሀነትንና ዜጎች ያበረከቱትን አስተዋጾ ይዘከራል።



በላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ በቶማስ ጀፈርሰን ህንጻ ውስጥ የሚገኝ ታላቁ አዳራሽ



የዩኤስ የእጽዋት ጥብቅ ማእከል

## ጠቃሚ ሊንኮች

*(ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድረ ገጾች በእንግሊዘኛ የተዘጋጁ ናቸዉ)*

**የዩኤስ ካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል፡-** www.visitthecapitol.gov

**የካፒቶል አርክቴክት፡-** www.aoc.gov

**የዩኤስ ሴኔት፡-** www.senate.gov

**የዩኤስ የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት፡-** www.house.gov

**ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ፡-** www.loc.gov

**የዩኤስ የእጽዋት ጥብቅ ማእከል፡-** www.usbg.gov

**ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-** www.supremecourt.gov

**ስሚሶኒያን፡-** www.smithsonian.com